# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

# 9ኛ ክፍል

አዘጋጅ፡- ፕሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- አቶ ዓባይ ተስፋዬ

ቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ፣ አቶ አማረ አያሌው

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ምልክት ቋንቋ፡- አቶ አማረ አያሌው

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

## ማውጫ ገጽ


ምዕራፍ አንድ:

የምልክት ቋንቋ ምልዑነት---------- 2

ምዕራፍ ሁለት፡

የምግብ ምንጮች ---------- 12

ምዕራፍ ሦስት፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ እሴቶች ---------- 22

ምዕራፍ አራት፡

የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ መንገዶች ---------- 33

ምዕራፍ አምስት፡

መስማት የተሳናቸው ባህል መገለጫ ባሕርያት ---------- 44

ምዕራፍ ስድስት፡

ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ መንገዶች ---------- 54

ምዕራፍ ሰባት፡

ውጤታማ የአጠናን ዘዴ ---------- 63

ምዕራፍ ስምንት፡

የከተሞች ታሪካዊ ጠቀሜታ ---------- 73

ምዕራፍ ዘጠኝ፡

የንብ አካል ክፍሎችና ተግባራቸው ---------- 82

ምዕራፍ አስር፡

የመረጃ አስተማማኝነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች ---------- 91

## መግቢያ

ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት መነሻ ምክንያት የሆነው የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ (ኢምቋ) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት መልክ እንዲሰጥ የታሰበው ሃሳብ ነው። ይህም መጽሐፍ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ኢምቋን እንዲማሩ በመማሪያነት እንዲያገለግል ነው።

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአስር ምዕራፎች ተከፋፍሎ ነው። እያንዳንዱ ምዕራፍ በቁልፍ ምልክቶች ይጀምርና፣ በመቀጠል አምስት ክፍለ ትምህርቶችን ይይዛል። የቁልፍ ምልክቶች ዓላማ፣ ተማሪዎች ወደ ምንባቦችና መልመጃዎች ከመምጣታችሁ በፊት፣ ቁልፍ ምልክቶችን አውቃችሁ እንደ መሸጋገሪያ ድልድይ እንድትጠቀሙባቸው ለማገዝ ነው።

ከቁልፍ ምልክቶች ቀጥሎ ክፍለ ትምህርት አንድ ተቀምጧል። የዚህ ክፍለ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ ደግሞ ተማሪዎች የየምዕራፉን አጠቃላይ ጭብጥ በስዕላዊ ገለፃ መልክ እንድትረዱት ለመርዳት ይሆናል።

ከዚያም ክፍለ ትምህርት ሁለት ይከተላል። ይህ ክፍለ ትምህርት፣ ምንባቦችንና የምንባቦችን መልመጃዎች ይዟል። የየምንባቦቹ መልመጃዎች የትኩረት አቅጣጫ ተማሪዎች የምንባቦችን ፍሬ ነገሮች እንድትረዱትና፣ በራሳችሁ የኢምቋ አጠቃቀም አማካኝነት የተረዳችሁትን እንድትገልጹ በማስቻል ላይ ነው። ክፍለ ትምህርት ሦስት የቡድን መልመጃዎች የተካተቱበት ነው።

ተማሪዎች ከምንባቡ በተወጣጡ ምልክቶች ላይ ተመስርታችሁ የራሳችሁን ዐረፍተ ነገር እንድትሰሩ ነፃነት ይሰጣችኋል። እንዲሁም ተማሪዎች ከምንባቡ ጋር በተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በቡድን ሆናችሁ የክፍል ውስጥ ውይይት እንድታካሂዱ የውይይታችሁን ውጤት እንድታቀርቡ ያስችላችኋል። ቀጥሎም ክፍለ ትምህርት አራት ይቀርባል።

ምልክቶች ሲሰሩ በዘፈቀደ ሳይሆን በመሰረታዊ የምልክቶች ባህርያት ላይ ተመስርታችሁ መሆን እንዳለበት የግንዛቤ አቅጣጫ እንዲሰጥ ነው።

በጨረሻም ክፍለ ትምህርት አምስት የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ምስረታ በሚል ልምምድና መልመጃዎች የያዘ ነው። የዚህ ክፍለ ትምህርት አስፈላጊነትም ተማሪዎች በንግግር ቋንቋና በኢምቋ መካከል ያለውን የዐረፍተ ነገር ሰዋስዋዊ አወቃቀር ልዩነት ግንዛቤ ማሳደግ ይሆናል። ይህ ምዕራፍ ተማሪዎችን በኢምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን ባለቤቶች፣ ግሶች፣ ተሳቢዎች፣ ቅጽሎች፣ ተውሳከ ግሶችና መስተዋድዶች የመለየት ክሂሎት እንድታዳብሩ ይረዳችኋል። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ኢምቋዐረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ። ገላጭ ዐረፍተ ነገር፣ ትዕዛዛዊ ዐረፍተ ነገር፣ ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገር እና የመሳሰሉት ምን መልክ እንዳላቸው መሰረታዊ ግንዛቤ እንድትጨብጡ መንገድ ይከፍትላችኋል።